የ2016 በጀት ዓመት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ



ነሐሴ 2015 ዓ.ም
ፋይናንስ ቢሮ
አዲስ አበባ



የዜጎች በጀት መረጃ ዝግጅት ቡድን አባላት

ማውጫ

የቢሮ ኃላፊ መልዕክት **4**
ምስጋና **6**
1. መግቢያ **7**
1.1. የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ ምንነት **7**
1.2. መንግስት የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድን ለምን ያዘጋጃል? **7**
2. ስለመንግስት በጀትና የበጀት አሰራር (አስተዳደር) ስርዓት **7**
2.1. የመንግስት በጀት ምንነትና አስፈላጊነት 7
2.2. የመንግስት በጀት ዝግጅትና አፈጻጸም ሂደት 8
2.2.1. የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ ዝግጅት (የፋይናንስ ዕቅድ ዑደት) 8
2.2.2.የበጀት ዑደት 9
3. ዜጎች በበጀት ዝግጅት ሂደት እንዴት ይሳተፋሉ 12
4. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2016 በጀት ዓመት በጀት **14**
4.1. የከተማ አስተዳደሩ በጀት እንዴት ነው የተዘጋጀው? 14
4.2. ከ2016-2018 በጀት ዓመት የገቢ ትንበያ 15
4.3. ከ2016-2018 በጀት ዓመት የወጪ ትንበያ 16
4.4. የከተማው አስተዳደር ለ2016 በጀት ዓመት የጸደቀ በጀት 16
4.5. የከተማ አስተዳደሩ የበጀት ምንጮች 17
4.6. የከተማ አስተዳደሩ የ2016 የበጀት ድልድል 17
4.7. ገቢን ከማሳደግና ወጪን ከመቆጠብ አኳያ የተወሰዱ አዳዲስ የፖሊሲ እርምጃዎች **22**
የበጀትና ፋይናንስ ቴክኒካል ቃላቶችና ሀረጎች መግለጫ **23**
ለበለጠ መረጃ፣ **27**

የቢሮ ኃላፊ መልዕክት



አቶ አብዱልቃድር ሬድዋን

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር በተለይ ከለውጡ በኋላ የከተማችንን ነዋሪዎች ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማረጋገጥ የ10 ዓመት እና የ5 ዓመት ፍኖተ ብልጽግና ዕቅድ በማቀድ ባለፉት ዓመታት ሰው ተኮር የሆኑ የልማት እንቅስቃሴ በማከናወን የነዋሪውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በዘላቂ ለመፍታት ጥረት ተደርጓል። የበጀት ምደባውም በዋናነት ለዘላቂ ልማት ላይ አተኩሮ በመመደብ የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማረጋገጥ አበረታች ውጤት በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ማስመዝገብ ተችሏል። ይህንን ተከትሎ የከተማው የማስፈጸም አቅምም በማደጉ የበጀት አጠቃቀም ከዕቅድ መሆን የተቀራረበ መሆን ችሏል።

በየዓመቱም በተሻለ የተቋም ግንባታ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት የተቻለ ሲሆን የካፒታል ፕሮጀክቶችም በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ በስራት በተሻለ ፍጥነት እና ጥራት ማስፈጸም ተችሏል።

በቀጣይም በከተማችን የተመዘገበውን የኢኮኖሚ ዕድገት በቀጣይነት ለማረጋገጥ በአሁን ጊዜ የሀገራቱን የማክሮ አኮኖሚ በዘላቂነት ለማረጋጋት የተወጠነውን የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳዎችን እውን ለማድረግ መንግስት በሁሉም ደረጃ በሚከናወኑ ተግባራት ላይ የዜጎች ተሳትፎንና ግልጽነትን በመተግበር የተጠያቂነት ስርዓቱ እንዲሰፍን እየሰራ ይገኛል። ለዚህም ማረጋገጫ የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ሪፎርም አንድ አካል የሆነውን የፋይናንስ ግልፅነትና ተጠያቂነት ስርዓት ትግበራ ላለፉት ዓመታት በክፍለ ከተሞች እና በማዕከል አገልግሎት ሰጪ (ትምህርት፣ጤናና የስራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ተቋማት ውስጥ ተፈጻሚ በማድረግ ማህበረሰቡ የታቀደውን

ወጪና ገቢ አፈጻጸሙን በቀላሉ በመከታተልና በተመዘገቡ ውጤቶች ላይም የተጠያቂነት ስርዓቱ ተግባራዊ እንዲሆን በመሰራቱ መልካም ውጤት ሊመዘገብ ችሏል።

ይህንኑ የግልጽነትና ሁለንተናዊ የዜጎች ተሳትፎን በማጠናከር በመንግስት በጀት አፈጻጸም ላይ የተጠያቂነት ስርዓቱ ተፈጻሚነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል በፋይናንስ ቢሮ ለ2016 በጀት ዓመት የጸደቀው በጀት መሰረት በማድረግ ሁሉም የከተማው ነዋሪ በቀላሉ ተረድቶት በትግበራ ሂደቱ ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆን የሚያስችል የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ አዘጋጅቶ አሰራጭቷል። በጀቱ የ10 (አስር) ዓመት እና የ5 ዓመት የከተማውን የልማት ዕቅድ እንዲሁም በአገር ደረጃ የተያዙ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳዎችን በመተግበርና ለዜጎች ሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ለድህነት ቅነሳና አጠቃላይ አካታች ዕድገትን ለማምጣት ታሳቢ ያደረገ ነው።

ስለሆነም ይህ የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ በከተማ አስተዳዳሩ ህግ-አውጪው በጸቀደው የመንግስት የገቢና የወጪ ዕቅዶች ውስጥ የተካተተውን በጀት ማህበረሰቡ በቀላሉ ተረድቶና ተጠቅሞ በመንግስት የልማት ስራዎች ላይ ተሳትፎውን በማጠናከር የተጠያቂነት ስርዓት ማስፈን እንዲቻል ሚናውን እንዲወጣ ጥሪዬን ማስተላለፍ እወዳለሁ።

ምስጋና

ይህ የ2016 የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ ዝግጅት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ የበላይ አካላት አመራር በመስጠታቸው ፣ የዜጎች በጀት ሰነድ ዝግጅት ግብረ ኃይል መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ትልቁን ድርሻ ለተወጡት (የፊስካል ፖሊሲ እና የገቢ ጥናት ፣ የበጀት ዝግጅት እና አስተዳደር ፣ የመንግስት ፋይናንስ ዳይሬክቶሬቶች ፣ በቻናል አንድ ፕሮግራም ማስተባበሪያ የፋይናንስ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት እና የማህበራዊ ተጠያቂነት ዩኒቶች) የላቀ ምስጋና ማቅረብ እንወዳለን። በተጨማሪም በረቂቅ ሰነዱ ላይ ሀሳቦችን እና አስተያየቶችን ለሰጡ ባለድርሻ አካላት ምስጋናችን እናቀርባለን።

1. መግቢያ

የከተማ አስተዳደሩ የበጀት ስርዓት መንግስት በፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት የሚከናወኑ ተግባራትንና የማስፈጸሚያ ሀብትን አመጣጥኖ የሚያቅድበት ነዉ። በዚህም የመንግስት በጀት የሚያመለክተዉ መንግስት በበጀት ዓመቱ የሚሰበስበዉን ግብርና ሌሎች ገቢዎች፣ ለዜጎች የሚቀርቡ አገልግሎቶችን ማሟላት የሚያስችል የኢኮኖሚ ዕድገቱን ማፍጠንን፣ ተጨማሪ የስራ ዕድሎችን የሚፈጥርበት፣ የመሰረተ ልማቱን የሚያስፋፋበትና ድህነትንና ኢፍትሓዊነትን የሚያጠፋበት ሂደት ሲሆንኔ እነዚህን ዉሳኔዎች ተፈጻሚ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ ጥቅም ላይ እንዲዉል የተፈቀደዉን በጀት ለሁሉም ሊገባ በሚችል መልኩ የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድን በማዘጋጀናት ተደራሽ በማድረግ የዜጎችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ማድረግ ነው።

1.1. የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ ምንነት

የዜጎች በጀት ሰነድ ማለት ነዋሪው ህብረተሰብ መንግስት ከተለያዩ የገቢ ምንጮች በዋናነት ከታክስ ሰብስቦ የህብረተሰቡን የልማትና የአስተዳዳር ወጪዎች ለመሸፈን የሚያወጣው ወጪ አመዳደብ እና አጠቃቀምን ለህብረተሰቡ ቀለል ባለ አቀራረብ የሚሳይ ሰነድ ነው።

ይህ በፋይናንስ ቢሮ ተዘጋጅቶ ለዜጎች የሚቀርበው የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ የመንግስት በጀት ሂደት ማለትም የበጀት ዝግጅትን፣ በጀትን ማጽደቅ፣ በጀትን ስራ ላይ ማዋልንና ስራ ላይ የዋለን በጀት እንዴት ቁጥጥር እንደሚደረግና በእያንዳንዱ ሂደት ኃላፊነት የተሰጠው አካልና የስራ ድርሻ ምን እንደሆነና ዜጎችም በዚህ የበጀት ሂደት እንዴትና መቼ መሳተፍ እንዳለባቸው በጥቅል በማመልከት በ2016 በጀት ዓመት የዜጎችን ቅድመ-ፍላጎቶች እና የከተማው አስተዳደሩ የትኩረት አቅጣጫ መሰረት የተመደባውን በጀትና በበጀቱ የሚከናወኑ አንኳር ጉዳዮችን ለከተማ ነዋሪዎች/ዜጎች የሚያስረዳ ነው።

1.2. መንግስት የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድን ለምን ያዘጋጃል?

ዜጎች ስለ መንግስት በጀት ምንነትና አሰራር በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው መንግስት በሚመድበውና ወጪ በሚያደርገው በጀት ላይ በሂደቱ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል ነው።

2. ስለመንግስት በጀትና የበጀት አሰራር (አስተዳደር) ስርዓት

2.1. የመንግስት በጀት ምንነትና አስፈላጊነት

2.1.1.የመንግስት በጀት ስንል ምን ማለታችን ነው?

የመንግስት በጀት በአንድ የበጀት ዓመት (ከሐምሌ 1-ሰኔ 30) የሚፈጸም እና ስለ መንግስት ገቢና ወጪ የሚተነበይበት ሰነድ ሲሆን ይህም ሁሉም የመንግስት ባለበጀት መስሪያ ቤቶች ከተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት አንጻር ሊያሳኩ ያስቀመጡትን ዓላማ እንዴትና በምን ያህል ሀብት እንደሚያከናውኑ በግልጽ የሚያሳይ ነው። የበጀት ሰነዱም በሚመለከተው በህግ-አውጭ አካል ከጸደቀ በኋላ ስራ ላይ ይውላል።

2.1.2.የመንግስት በጀት ለሁለንተናዊ ልማት የሚጫወተው ቁልፍ ሚና

የመንግስት በጀት የፖሊሲ ማስፈጸሚያ መሣሪያ ነው። ይህ ማለት መንግስት የህዝቡን የልማትና መልካም አስተዳደር ጥያቄ ለመመለስ የሚወጥናቸውን ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ተግባራዊ የሚያደርገውና የመንግስት አገልገሎቶችን ለህዝቡ የማቅረብ ኃላፊነቱን የሚወጣው በበጀት አማካኝነት ነው። በመንግስት የፖሊሲ ሰነዶች የተቀመጡ የህዝቡን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የተወጠኑ

ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ትልሞች ወይም ግቦች በበጀት ካልተደገፉ በተጨባጭ የማይታዩ የመንግስት ምኞቶች ሆነው ነው የሚቀሩት። ለዚህም ነው በመንግስት በጀት አስተዳደር ስርዓት ግልጽነትና ተጠያቂነት ለማስረጽ ከፍተኛ ርብርብ የሚደረገው።

2.1.3.የመንግስት በጀት ለምን ይዘጋጃል?

መንግስት የዜጎችን ፍላጎት ሁሉ በአንድ ጊዜ ለማሟት የሀብት ውስንነት ስላለበት ለዜጎች በቅድሚያ መቅረብ ያለባቸውን አገልግሎቶች በመለየትና ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሀብት ከየትና እንዴት ሊገኝ እንደሚችል ለመወሰን በጀት ያዘጋጃል። በመሆኑም በበጀት ዝግጅት ቅድሚያ የተሰጣቸውና በበጀት የተደገፉ ተግባራት የመንግስትን ቁልፍ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎችን የሚጠቁሙ ይሆናሉ ማለት ነው።

2.2. የመንግስት በጀት ዝግጅትና አፈጻጸም ሂደት

የመንግስት በጀት ዝግጅት ሂደት መነሻ የሚያደርገው የከተማ አስተዳደሩን የልማት ፖሊሲንና በዚሁ መነሻነት የሚዘጋጁ የልማት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ሲሆን ሂደቱ በውስጣቸው በርካታ ተግባራትን ያካተቱ ደረጃዎችን (ዑደቶችን) ያካትታል። የመጀመሪያው የመካከለኛ ዘመን የፋይናንስ ዕቅድ (የሶስት አመት ተንከባላይ የወጪ ግምት) የሚዘጋጀበት (የዕቅድ ዑደት) ሲሆን ሁለተኛው ዓመታዊ በጀት የሚዘጋጅበት ሂደት (የበጀት ዑደት) ነው።

2.2.1. የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ ዝግጅት (የፋይናንስ ዕቅድ ዑደት)

የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ /Medium Term Expenditure Framework/ በመንግስት የልማት ፖሊሲዎች ፣ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች እና በጀት መካከል ያለውን ትስስር በማጠናከር የልማት ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል በየዓመቱ የሚታደስ የ3 ዓመት ተንከባላይ የወጪ ዕቅድ /Rolling plan/ ሲሆን ይህም የሀብት ምደባ፣ የወጪ ቁጥጥርና አጠቃላይ የመንግስት የፊስካል ፖሊሲ ውጤታማነትን ለማሻሻል እንዲሁም የሀብት ምደባን ከተጠያቂነት ጋር ለማስተሳሰር የሚረዳ ጠቃሚ የዕቅድ መሳሪያ ነው። ከዚህ ባሻገር የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ የፊስካል ተተንባይነትንና ግልጸኝነትን ስለሚያካትት መንግስት ፖሊሲዎችን ለማስፈጸም ያለውን ቁርጠኝነት ያንጸባርቃል።

የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ መሠረታዊ ዓላማ የበጀት ዝግጅት ከአንድ ዓመት ዕይታ ወደ መካከለኛ ዘመን ዕይታ በማሸጋገር፣ በጀት የመንግስትን የልማት ፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫ መሠረት ባደረገ መልኩ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎችና በየዘርፉ ለሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች እንዲመደብ በማድረግ እና የሀብት (ለእነዚህ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገዉን በጀት) አቅርቦት ተተንባይነት በማሻሻል በመንግስት ፖሊሲ (የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅዶች) መካከል ትስስርን ከመፍጠር ባለፈ የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማረጋገጥ ነዉ።

የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ ዝግጅት ሂደት ሁለት ዐብይ ተግባራትን የሚያካትት ሲሆን የመጀመሪያው በመካከለኛ ዘመን (ከ3-5 ዓመታት) የሚኖረውን የገቢና ወጪ መጠን ለመተንበይ ወሳኝ የሆኑ የማክሮኢኮኖሚ (አጠቃላይ የምርት ዕድገት፣ የዋጋ ግሽበት፣የስራ ዕድል ምጣኔ...) እና የፊስካል (የመንግስት የገቢና ወጪ ፖሊሲ) ታሳቢዎችን መተንተን ሲሆን ሁለተኛው ታሳቢዎቹን መሠረት በማድረግ ትንበያውን ማካሄድ ነው።

2.2.2.የበጀት ዑደት

በጀት የሚከተሉትን አራት ዑደት/ደረጃዎች ያካተተ ዑደት አለው።

(ሀ) በጀት ማዘጋጀት (Executive Preparation)

በአስፈጻሚው አካል የሚከናወነው የበጀት ዝግጅት የመጀመሪያው ደረጃ ሲሆን ይህም የከተማ ማዕከል መስሪያ ቤቶች፣የክፍለ ከተማ የድጎማ በጀት ማከፋፈያ ቀመር ማዘጋጀትን፣ የድጎማውን ግምት ማስታወቅን፣ የበጀት ጥሪ ማስተለለፍን፣ የበጀት ጥያቄ ማቅረብን፣ የተደገፈ በጀት ዝግጅትን እና የተደገፈ በጀት በካቢኔ ማጽደቅ የሚያካትት ነው።

(ለ) በሕግ አውጪ አካል ማጸደቅ (Legislative Approval) ፣

በህግ አውጪው (በከተማው ም/ቤት) የሚከናወነው በጀት የማጽደቅ ተግባር የበጀት ዑደት ሁለተኛው ደረጃ ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት የሚያካትት ነው።

- **የክፍለ ከተማ የድጎማ በጀት ማከፋፈያ ቀመር ማጽደቅ፣**
- **የጸደቀውን በጀት አዋጅ ረቂቅ ማጽደቅ /ለምክር ቤቱ የተላከው በጀት በምክር ቤቱ የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ኮሚቴ ተገምግሞ እንዲጸድቅ ለምክር ቤቱ ጉባኤ ይቀርባል፣**
- **የጸደቀውን በጀት ሥራ ላይ እንዲውል መፍቀድ /ምክር ቤቱም በጀቱን መርምሮ ያፀድቃል። በክፍለ ከተማም ይህ ተግባር ተመሳሳይ ይከናወናል።**


(ሐ) በአስፈፃሚ አካል ሥራ ላይ ማዋል (Executive Implementation)

ይህ የበጀት ዑደት ሦስተኛው ደረጃ ሲሆን በህግ አውጪው (በም/ቤት) የጸደቀው በጀት በአስፈጻሚው አማካኝነት ሥራ ላይ የሚውልበት ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ሁለት ዐብይ ተግባራት ማለትም የታወጀውን በጀት ማስታወቅን እና የታወጀውን በጀት በሥራ ላይ ማዋልን ያካትታል፡-

(መ) ኦዲት እና ግምገማን (Audit)

ኦዲት በህግ አውጪው አካል የጸደቀው በጀት ለታለመለት ዓላማ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን የማረጋገጥ ሥራ የሚከናወንበት የበጀት ዑደት የመጨረሻው (አራተኛው) ደረጃ ነው። ይህም ወጪዎች/ ክፍያዎች፣በጀት፣ ግዢ እና ንብረት አስተዳዳሩ በመንግስት ፋይናንስ አስተዳዳር፣ በመንግስት ግዢ አዋጅ እና የንብረት አስተዳዳር አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያዎች መሰረት ወጪው እና የንብረት አስተዳዳሩ መከናወን የማረጋገጥ ተግባር ነው።

ምስል 1፡ የበጀት ዑደት(Budget Cycle)



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2016 በጀትም ከላይ በቀረበው ዑደት መሰረት የተዘጋጀ ነው።

2.2.2.3 የፋይናንስ የጊዜ ሠሌዳ

የፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳ ማለት የፋይናንስ ዕቅድ ዝግጅትና የበጀት ሂደት መቼ ተጀምሮ መቼ እንደሚጠናቀቅ የሚያመለክት ሰነድ ነው። በሌላ አገላለጽ የፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳ ከታች በሠንጠረዥ 1 በተገለጸው መሠረት በተራ ቁጥር 2 የተገለጸው የፋይናንስ ዕቅድ ዝግጅት እና በአራቱ የበጀት ዑደት ደረጃዎች የተካተቱት ተግባራት መቼና በማን እንደሚከናወኑ በዝርዝር የሚያሳይ መመሪያ ነው።

ሠንጠረዥ1፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳ

ተ.ቁ	ዑደት/ክፍል/ደረጃ	በኢትዮጵያ አቆጣጠር	ኃላፊነት የተሰጣቸው መ/ቤቶች
	የዕቅድ ዑደት/ደረጃ		
1	ከአንድ ዓመት በላይ የሆነ ዕቅድ	ሃምሌ1-ነሃሴ30	ፕላንና ልማት ኮሚሽን
2	ከአንድ ዓመት በላይ የሆነ ፕሮግራም	መስከረም15-ታህሳስ 30	ፋይናንስ ቢሮና የመንግስት መ/ቤቶች
3	ዓመታዊ የፋይናንስ ዕቅድ	ጳጉሜ1-ታህሳስ 30	ፋይናንስ ቢሮ
	የበጀት ዑደት ክፍል/ደረጃ/		
	ሀ.በአስፈጻሚ አካል የሚደረግ ዝግጅት		
1	የበጀት ዝግጅት	መስከረም21-መጋቢት7	የመንግሥት መ/ቤቶች
2	የክፍለ ከተማ የድጎማ በጀት ማከፋፈያ ቀመር ዝግጅት	መስከረም 20-ህዳር5	ፋይናንስ ቢሮ
3	የድጎማውን ግምት ማስታወቅ	ታህሳስ 30-ጥር 7	ፋይናንስ ቢሮ
4	የበጀት ጥሪ	ታህሳስ 30-ጥር 29	ፋይናንስ ቢሮና
5	የበጀት ጥያቄ	ጥር 30-መጋቢት 22	የመንግሥት መ/ቤቶች
6	የተደገፈ በጀት ዝግጅት	መጋቢት 23-ግንቦት 29	ፋይናንስ ቢሮ
7	የተደገፈ በጀት ማጽደቅ	ግንቦት 30-ሰኔ 13	ካቢኔ
	ለ.በህግ አውጪው መጽደቅ		
8	የክፍለከተማ የድጎማ በጀት ማከፋፈያ ቀመር ማጽደቅ	ህዳር 7-ታህሳስ 6	ካቢኔ
9	የጸደቀውን በጀት አዋጅ ረቂቅ ማጽደቅ	ሰኔ 14-ሰኔ 30	ምክር ቤት
10	የጸደቀውን በጀት ሥራ ላይ እንዲውል መፍቀድ	ሰኔ14-ሰኔ 30	ምክር ቤት
	ሐ.በአስፈጻሚ አካል ሥራ ላይ ማዋል		
11	የታወጀውን በጀት ማስታወቅ	ሃምሌ1-ሃምሌ 8	ፋይናንስ ቢሮ
12	የታወጀውን በጀት በሥራ ላይ ማዋል	ሃምሌ 9-ሰኔ 30 በሚቀጥለው በጀት ዓመት	የመንግሥት መ/ቤቶች

ምንጭ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የበጀት ማኑዋል 2006 ዓ.ም

3. ዜጎች በበጀት ዝግጅት ሂደት እንዴት ይሳተፉ

የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት እና የከተማ አስተዳደሩ ቻርተር ዜጎች በመንግስት ሁለንተናዊ ተግባራት ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይደግፋል።

- የኢፌዲሪ ህገ-መንግሰት በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 እንደተገለጸዉ የመንግስት አሰራር ግልፅ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት። ማንኛውም ኃላፊና የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጎድል ተጠያቂ ይሆናል። በአንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ 6 የሀገር ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሚዘጋጁበት ወቅት መንግስት ሕዝቡን በየደረጃው ማሳተፍ አለበት። የሕዝብንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት።
- የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 በአንቀጽ 7 ን/አንቀጽ 1 እና 3 ነዋሪዎች ስለከተማዉ የሚወሰኑ ጉዳዮችን በሚመለከት መረጃ የማግኘት፣ ሀሳብና ጥያቄ የማቅረብ እና መልስ የማግኘት መብት እንዳላቸዉ እንዲሁም የከተማዉ አስተዳደር ፖሊሲ፣ በጀት የሥራ ዕቅድና መመሪያ ለነዋሪዎች ይፋ መሆን እንዳለበት፤ በተመሳሳይም በአንቀጽ 59 ን/አንቀጽ 2 የከተማዉ በጀት በግልጽና ነዋሪዉን በሚያሳትፍ መልኩ መዘጋጀት እንዳለበት ይደነግጋል።
- በከተማ አስተዳደሩ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓት መተግበሪያ መመሪያ ቁጥር 05/2011 ክፍል አንድ ተራ ቁጥር 5 (1) እንደተገለጸዉ ሁሉም የመንግስት ባለበጀት መስሪያ ቤቶች የተሟላ፣ ቀላልና ወቅታዊ የሆነ የበጀት መረጃ ለዜጎች ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

ዜጎች በሚከተሉት መንገዶች በበጀት ሂደት ሊሳተፉ ይችላሉ፤



1. በተወካዮቻቸው አማካኝነት (On their representatives)

የህግ አውጪዉ/የህዝብ ተመራጮች አስፈጻሚዉን አካል በእቅድ ያቀረበዉን የወጪና የገቢ አሰባሰብ እንዲሁም እቅዱን ለማስፈጸም በሰጠዉ ውሳኔና የተገኘውን ዉጤት መነሻ በማድረግ በጥልቀት ሊመረምርና ኃላፊነቱን ባልተወጣ ጊዜ ተጠያቂ ያደርጋል።



2. ቅድመ-በጀት ውይይት (Pre-budget discussion)

- የቅድመ በጀት ውይይት- ህዝቡ የመንግሰትን የወጪና የገቢ እቅድ እንዲያዉቅ በማድረግ የበጀት ዓመቱ በጀት ከመጽደቁ በፊት ለበጀት አፈጻጸም ዉጤታማነት ግብአት ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን ከህዘቡ እንዲያገኝ እድል ይሰጣል፤
- የከተማዉ ምክር ቤት በአስፈጻሚ አካላት የቀረበለትን በጀት ከማጽደቁ በፊት የሲቪክ ማህበራት፤ ግለሰቦች፤ ተቋማትና ሌሎች የሚመለከታቸዉ አካላት በቀረበዉ ረቂቅ በጀት ላይ ሀሳብና አስተያየት እዲያቀርቡ በሚደረግ ሂደት ዜጎች መሳተፍ ይችላሉ፤



3. በመንግስት ተቋማት የህዝብ ተሳትፎ መድረኮች(public participation)

የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች ከህብረተሰቡና ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በተቋማቸው የሩብ አመትና ዓመታዊ የበጀትና እቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ግምገማ በሚደረግበት ወቅት ዜጎች መሳተፍ ይችላሉ፤



4. ማህበረሰብ አቀፍ የልማት ኮሚቴዎች (Community Based Development Committees)

በመንግስት አስፈጻሚ አካላትና በማህበረሰቡ ተነሳሽነት በተመረጡና በተቋቋሙ የልማት ኮሚቴዎች አማካኝነት ዜጎች ተሳታፊ ይሆናሉ፤



5. ሁለንተናዊ የዜጎች ተሳትፎ ስልቶች (Inclusive citizen participation strategies)

የግልጽነትና ማህበራዊ ተጠያቂነት አሠራር ስርዓትን በህብረተሰቡ ዘንድ በማስረጽና የማህበረሰቡን አቅም በመገንባት፡

– ዜጎች የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶችን ይለያሉ። ይህን መሠረት በማድረግም ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዘው የተለዩ የቅድሚያ ቅድሚያ ችግሮች ትኩረት እንዲያገኙ ለማድረግ የአገልግሎት ተጠቃሚው ማህበረሰብ በበጀት ዝግጅት ሂደት ላይ በንቃት ይሳተፋል።

በመሆኑም የከተማው አስተዳደር የ2016 በጀትም ከላይ በተገለፀው መሰረት ህብረተሰቡን በማሳተፍ ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው።

4. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2016 በጀት ዓመት በጀት

4.1. የከተማ አስተዳደሩ በጀት እንዴት ነው የተዘጋጀው?

የከተማው አስተዳደር ከ2013 እስከ 2022 ዓ.ም ያለውን ጊዜ የሚሸፍን የአስር ዓመት ዕቅድ (ፍኖተ ብልጽግና) ከማዘጋጀቱም ባለፈ ለተግባራዊነቱ የአምስት ዓመት (ከ2013 እስከ 2017) የልማት ፕሮግራም ነድፎ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። በእነዚህ የረዥምና በመካከለኛ ጊዜ የልማት ዕቅድ ሰነዶች ውስጥ የተቀመጡቱት ግቦች ስኬት የሚወሰነው ለተፈጻሚነታቸው በሚመደበው በጀት መጠንና ውጤታማ አጠቃቀም ነው። ለዚህም ፖሊሲንና በጀትን ማስተሳሰርን መሠረት ያደረገ የበጀት ድልድል/ምደባ እና አጠቃቀም ስርዓትን መዘርጋት ወሳኝ ነው።

በዚህም መሠረት የከተማው ውስን ሀብት (በጀት) በከተማ አስተዳደሩ የረዥምና የመካከለኛ ጊዜ የልማት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ቅድሚያ የተሰጣቸውን ግቦች ከማሳካት አኳያ የተቃኘና አጠቃቀሙም ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የ3 ዓመት ተንከባላይ የፋይናንስ ዕቅድ ማለትም የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ /Medium Term Expenditure Framework/ የመንግስት የበጀት አስተዳደር ስርዓት አካል ሆኖተግባራዊ እያደረገ ይገኛል።

የከተማ አስተዳደሩ ውስን የሆነውን የከተማዋን ሀብት ድልድል ከከተማዋ የልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር ይበልጥ ለማስተሳሰር የበጀት ዝግጅቱን ከአንድ ዓመት እይታ ወደ መካከለኛ ዘመን እይታ በማሸጋገርና የከተማው አስተዳደር ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች በመመደብ በየዘርፉ የሚተገበሩ ፕሮግራሞች ወጥነት እንዲኖራቸው በማድረግ አስፈላጊውን የመሰረተ ልማትና መሰረታዊ አገልግሎት በተፋጠነ ሁኔታ ለማቅረብ የሚያስችል ስርዓት የመዘርጋት ሂደት በተጠናከረ መልኩ በማካሄድ ላይ ይገኛል።

በዚህም መሠረት የከተማው የ2016 በጀት ዓመት የበጀት ዝግጅት መነሻ ያደረገው የከተማ አስተዳደሩን የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ አካል የሆነውን የ3 ዓመት (የ2016-2018 በጀት ዓመት) የገቢና ወጪ ትንበያ ሲሆን ይህም የሚከተሉትን የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ታሳቢዎችን መሠረት ያደረገ ነው።

- **የኢኮኖሚ ታሳቢዎች፡-** የቀጣዮቹን 3 ዓመታት የገቢ ትንበያ ታሳቢ መነሻ ካደረጋቸው ኢኮኖሚያዊ ታሳቢዎች አንዱ የኢኮኖሚ ዕድገት ነው። በዚህም መሠረት በሚቀጥሉት 3 ዓመታት (2016-2018) የከተማው አስተዳዳር ፈጣንና ቀጣይነት ያለው በአማካይ የ10 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ የተገመተ ሲሆን ዕድገቱ በታክስ ገቢ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር፣ የስራ ዕድል እንደሚፈጥር እና የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ እንደሚጨምር ታሳቢ ተወስዷል።

- **የፊስካል ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ታሳቢዎች**
  - የታክስ አሰባሰብ ስርዓቱ በሰው ኃይልና ዘመኑ ባፈራው ቴክኖሎጂ እንደሚጠናከርና በዚህም በየበጀት ዓመቱ በዕቅድ ከተያዘው የታክስ ገቢ 100% እንደሚሰበሰብ፣
  - የታክስ መሰረቱን የማስፋት ስራ እንደሚጠናከር፣
  - ከታክስ አሰባሰብ ጋር ተያይዞ የሚመለከታቸው አካላት በቅንጅት እንደሚሰሩ፣
  - በግብር ከፋዩ ዘንድ ግብርና ቀረጥ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል እንደሚዳብር፣
  - በውስጥም በውጭም ብልሹ አሰራር ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል፣
  - የከተማ አስተዳደሩ ለታክስ ገቢ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ውዝፍ ገቢ መሰብሰብ እና የህግ ማስከበር ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል፣

- የተጀመረውን የቤት ግብር ስርዓት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል እና የገቢ ማበልጸጊያ ጥናት ተግባራዊ እንደሚሆን ፣
- በታክስ አስተዳደሩ ረገድ ተግባራዊ ሊደረጉ የታቀዱ ማሻሻያዎች ለታክስ አሰባሰቡ የሚያደርጉት አስተዋጸኦ ግምት ውስጥ ገብቷል።

☛ **አጠቃላይ ፖለቲካዊ ታሳቢዎች፡-**ከፖለቲካዊ ሁኔታ አንጻር በከተማችን ያለው የፖለቲካ መረጋጋት ሁኔታ ቀጣይነት ባለው መልኩ እየተሻሻለና እየተጠናከር እንደሚሄድ ... በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የነበረውን ጦርነት በስምምነት መፍታት መቻሉ እና ሰላምን ለማዝለቅ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች እየታየ ያለው አንጻራዊ ሰላምና መረጋጋት እና የአገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ለከተማችን ዕድገት ቀጣይነት እንደሚኖረው እና የበለጠ እንደሚጠናከር ተወስዷል።

4.2. ከ2016-2018 በጀት ዓመት የገቢ ትንበያ

ከላይ የተገለጹትን ታሳቢዎች ግምት ውስጥ በማስገባት የከተማው ገቢ ከታች በሰንጠረዥ2 እንደተመለከተው በ2016፣ 2017 እና 2018 እንደቅደምተከተላቸው 40.21%፣ 19.68 % እና 22.20% ዕድገት እንደሚያሳይ ተተንብይዋል።

ሠንጠረዥ2፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የ2016-2018 በጀት ዓመት የገቢ ትንበያ (በቢሊየን ብር)

ተ.ቁ	በጀት ዓመት	2015 (ዕቅድ እንደ መነሻ)	2016	2017	2018
1	**የከተማ አስተዳደሩ የራስ ገቢ**	95.2	137.066	163.82	200.55
	የታክስ ገቢ	70.829	98.34	117.5	141.9
	ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች	11.53	17.7	19.43	25.26
	ከማዘጋጃ ቤት የሚገኝ ገቢ	12.57	21.026	26.87	33.41
	ካለፉት በጀት ዓመታት የተላለፈ	2			
2	**የፌደራል መንግስት የበጀት ድጋፍ**	3.115	3.221	4.08	4.62
	የውጭ አገር እርዳታ	0.21	0.177	0.29	0.3
	የውጭ አገር ብድር	2.642	2.84	3.55	4.02
	ከመንገድ ፈንድ	0.263	0.204	0.24	0.3
	ጠቅላላ ድምር	100.05	140.29	167.90	205.17
	ዕድገት በ%		40.21	19.68	22.20

ምንጭ፦ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ 2015 ዓ.ም

ከላይ በሰንጠረዥ 2 ለማሳየት እንተሞከረው ምንም እንኳን ከተማችን የተለያዩ የገቢ ምንጮች ቢኖሯትም ከፍተኛውን ድርሻ (70.09%) የሚይዘው የታክስ ገቢ ነው። በዚህም መሠረት የከተማዋን የኢኮኖሚ ዕድገት ከማስቀጠልና የነዋሪዎቿን የኑሮ ሁኔታ ከማሻሻል አኳያ ከታክስ የሚገኘው ገቢ የሚጫወተው ሚና ወሳኝነት አለው።

4.3. ከ2016-2018 በጀት ዓመት የወጪ ትንበያ

የከተማው ገቢ ከላይ በሰንጠረዥ 2 በተገለጸው ትንበያ መሠረት ዕድገት እንደሚያሳይ እና የሚከተሉት ታሳቢዎች እንደሚሟሉ ግምት ውስጥ በማስገባት የከተማው አጠቃላይ ወጪ በ2016፣ 2017 እና 2018 በጀት እንደቅደምተከተላቸው በ40.22 %፣19.68% እና 22.20% እንደሚያድግ ይገመታል።

- የከተማ አስተዳደሩ ራዕይ፣ ራዕዩን ለማሳካት የተነደፈው የ10 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫና ስትራቴጂክ ዕቅዱ በመነጨው የመጀመሪያው የአምስት የልማት ፕሮግራም ትኩረት የተሰጣቸው የልማትና መልካም አስተዳደር ግቦች፣
- ያለፉት 2 ዓመት (2013-2014) እና የ2015 የ9 ወራት የወጪ አፈጻጸም አዝማሚያ፣
- የከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ አካላት የአደረጃጀት ለውጥና ይህም በወጪ ላይ ሊያስከትል የሚችለው ተጽእኖ፣
- እያደገ የመጣ የማስፈጸም አቅም ግንባታ፣
- የዋጋ ግሽበት እና የነዋሪው ህዝብ አዳዲስ የልማት ፍላጎቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ሠንጠረዥ3 ፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የ3 ዓመት (2016-2018 በጀት ዓመት) የወጪ ትንበያ

ወጪ	2015 (መነሻ ዓመት)	2016	2017	2018	አማካይ ዕድገት (በመቶኛ)
የከተማው አጠቃላይ ወጪ በቢሊየን ብር	100.05	140.29	167.90	205.17	
መደበኛ ወጪ በቢሊየን ብር	46.33	62.29	96.09	92.54	
ዕድገት %		34.45	72.95	(3.69)	34.57
ካፒታል ወጪ በቢሊየን ብር	53.72	77.99	128.00	137.00	
ዕድገት %	61.52	45.18	64.11	7.03	38.77
የካፒታል ወጪ ከአጠቃላይ ወጪ የሚኖረው ድርሻ (በመቶኛ)	53.69	55.59	76.24	66.77	66.20

ምንጭ፦ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ 2015 ዓ.ም

4.4. የከተማው አስተዳደር ለ2016 በጀት ዓመት የጸደቀ በጀት

የከተማው የ2016 የጸደቀ በጀት ብር 140.29 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ ብር 62.29 ቢሊየን እና ካፒታል 77.99 ቢሊየን ተደልድሏል። ከአጠቃላይ ዓመታዊ በጀት ውስጥ ለማዕከል መስሪያ ቤቶች ብር 98.13 ቢሊየን ሲሆን ቀሪው ብር 42.15 ቢሊየን ለክ/ከተሞችና በሥራቸው ለሚገኙ ወረዳዎች የተመደበና በቀመር የተከፋፈለ ነው።

የ2016 የከተማው በጀት ዕድገት አዝማሚያ ሲታይ ካለፈው 2015 በጀት ዓመት ብር 40.23 ቢሊየን ወይም 40.21 በመቶ ዕድገት አለው።

4.5. የከተማ አስተዳደሩ የበጀት ምንጮች

በዚህ አንጻር ሁሉም ክልሎች እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከፌዴራል መንግስት በየዓመቱ ድጎማ በቀመር የሚያገኙ ሲሆን አዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ምንም ዓይነት ድጎማ የማታገኝና የራሷን ወጪ ከተማዋ ከምታመነጨው ሀብት የምትሸፍን ብቸኛ ከተማ ነች። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተሻሻለው የከተማው ማቋቋሚያ ቻርተር ቁጥር 361/1995 መሰረት

1. **ታክስ ገቢ/**Tax Revenue/ ቀጥታ ታክስ/Direct Taxes/ የግለሰብ ገቢ ግብር፣ የኪራይ ገቢ፣ የንግድ ትርፍ ገቢ ግብር፣ ዊዝ ሆልድ ታክስ…. / እና ቀጥታ ካልሆኑ ታክስ/ Indirect Taxes/ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ኤክሳይዝ ታክስ፣ ተርን ኦቨር ታክስ፣
2. **ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች** / Administrative fees and charges, Sales of Public Goods and Services/
3. **ማዘጋጃቤታዊ ታክስ ገቢ/**Municipal Taxes/ማዘጋጃቤታዊ ታክስ እና ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች
4. **የመንገድ ፈንድ-** /Road Fund/
5. **ዕርዳታ** /ከልማት አጋሮች ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ለትምህርት ፣ ለጤና …የሚገኝ /
6. **ብድር** /በተለይ ለውሃ፣ለመንገድ እና ትራንስፖርት / ናቸው።

4.6. የከተማ አስተዳደሩ የ2016 የበጀት ድልድል

4.6.1.የበጀት ድልድል ስርዓት

የከተማው አስተዳዳር በጀት የሚደለድልበት ስርዓት መነሻው የተሻሻለው የከተማው አስተዳዳር ማቋቋሚያ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 እና የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የፋይናንስ አስተዳዳር አዋጅ ነው።

በዚህ መሰረት በከተማ አስተዳዳሩን የጸደቀ የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ መነሻ በማድረግ ዓመታዊ የበጀት መመሪያ ይዘጋጃል። መመሪያው የሚያገለግለው ለቀጣይ በጀት ዓመት ብቻ ሆኖ በማክሮ-ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ/ MTEF/ ውስጥ የተቀመጡ ከሀብት አሰባሰብ እና ከወጪ አመዳደብና አጠቃቀም ጋር ያሉትን ዋና ዋና ጉዳዩችን ያካትታል።

4.6.2.ለማዕከል ባለበጀት ተቋማት የተመደበ በጀት

በከተማ ደረጃ ለሚገኙ የማዕከል መ/ቤቶች ለ2016 በጀት ዓመት ጠቅላላ ብር 98.13 ቢሊየን የጸደቀ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ ብር **28.79 ቢሊየን/ ለደመወዝ** 8.46 ቢሊየን ፣ ለስራ ማስኬጃ 15.84 ቢሊዮን 5.30 ቢሊየን ለመጠባበቂያ/ እና ለካፒታል ብር 69.33 ቢሊየን ብር ተደልድሏል።

4.6.3.የክ/ከተሞችና ወረዳዎች በጀት ድጋፍ (ድጎማ)

የክፍለ ከተሞች የ2016 በጀት ዓመት ጠቅላላ የተመደበ በጀት ብር 42.15 ቢሊየን **የተደለደለ** ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ በጀት ብር 33.49 ቢሊየን እና ለካፒታል ደግሞ ብር 8.65 ቢሊየን በመሆን ተደልድሏል። ለክፍለ ከተሞች ከተመደበው ጠቅላላ የካፒታል በጀት ውስጥ ብር 7.37 ቢሊየን የሚሆነው በዓላማ የተገደበ (ተለይተው ለተቀመጡ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚውል) በጀት ሲሆን ቀሪው ብር 1.28 ቢሊየን በዓላማ ያልተገደበ (በክ/ከተሞች ውሳኔ መሠረት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ፕሮጀክቶች የሚውል) በጀት ነው።

ሠንጠረዥ 4፡-የ2016 በጀት ዓመት የተፈቀደ ወጪ ዕቅድ እና ከአጠቃላይ ያለው ድርሻ

ተ.ቁ	የበጀት ዓይነት	የወጪ ዕቅድ (ቢሊየን ብር)	ከአጠቃላይ ያለው ድርሻ (%)
1	ጠቅላላ በጀት	140.29	100
2	ለከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ አካላት	98.13	69.95
2.1	ለመደበኛ ወጪ	28.79	20.52
2.1.1	ለደመወዝ	8.46	6.03
2.1.2	ለሥራ ማስኬጃ	15.84	11.29
2.1.3	ለመጠባበቂያ	5.3	3.78
2.2	ለካፒታል ወጪ	69.33	49.42
3	ለክ/ከተሞች የሚከፋፈል የበጀት ድጋፍ (ድጎማ)	42.15	30.04
3.1	መደበኛ ወጪ	33.49	23.87
3.1.1	ደመወዝ	21.2	15.11
3.1.2	ስራ ማስኬጃ	11.72	8.35
3.1.3	መጠባበቂያ	1.18	0.84
3.2	ካፒታል ወጪ	8.65	6.17
3.2.1	ጥቅል (በዓላማ ያልተገደበ) ድጋፍ	1.28	0.91
3.2.2	በዓላማ የተገደበ የበጀት ድጋፍ	7.37	5.25

ምንጭ፦ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ 2015 ዓ.ም

4.6.4.የ2016 የጸደቀ በጀት በዘርፍ

ከታች በሰንጠረዥ 5 ላይ እንደተመለከተው በ2016 በጀት ዓመት ከጸደቀ በጀት ውስጥ ከፍተኛው በጀት የተመደበው ለኢኮኖሚ ዘርፍ ብር 60.33 ቢሊየን ሲሆን አስተዳደራዊና ጠቅላላ አገልግሎት ብር 31.45 ቢሊየን፣ማህበራዊ ብር 28.69 ቢሊየን፣ ማዘጋጃቤታዊ ብር 10.04 ቢሊየን እና ሌሎች ብር 9.75 ቢሊየን ድርሻቸውን ይወስዳሉ።

ሠንጠረዥ 5 ፡- የ2016 በጀት ዓመት የጸደቀ በጀት በዘርፍ (በቢሊየን ብር)

ዘርፍ	የጸደቀ በጀት	ድርሻ (በመቶኛ)
አስተዳዳርና ጠቅላላ አገልግሎት	31.45	22.42
ኢኮኖሚ	60.33	43.01
ማህበራዊ	28.69	20.46
ሌሎች[1]	9.75	6.96
ማዘጋጃቤታዊ	10.04	7.16
ጠቅላላ ድምር	140.29	100.00

ምንጭ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ፋይናንስ ቢሮ 2015 ዓ.ም

ሌሎች* ለመጠባበቂያ ፣ድጎማ...

4.6.5. በወጪ ዕቅድ ትኩረት የተሰጣቸው ሴክተሮች/ዘርፎች

የከተማ አስተዳዳሩ የ10 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ለድህነትና የዜጎችን ቅድመ ፍላጎቶች መሰረት በማድረግ የከተማ አስተዳዳሩ በጀት በዋናነት ድህነት ተኮር ዘርፎች ላይ ያተኮረ ሲሆን በተለይም በውሃና ፍሳሽ፣ጤና፣ትምህርት ፣ስራ ዕድል ፈጠራ፣የመኖሪያ ቤትና ትራንስፖርት ላይ በማተኮር ሀገራችን ለማሳካት የገባችውን የዘላቂ የልማት ግቦችን ማዕከል ያደረገ ነው።

በዚህ መሰረት ባለፉት ሶስት ዓመታት/2013-2015/ ከ 2.648 ቢሊየን ብር በላይ ወጪ በማድረግ የስራ ዕድል ፈጠራ ስራዎች ተከናውኗል። ለወጣቱ እና ለሴቶች የስራ እድል ከመፍጠሩ ባሻገር በኢኮኖው ውስጥ ሚና እንዲኖራቸው ተደርጓል።

መንግስት ባለፉት ሶስት ዓመታት/2013-2015/ ከብር 26.201 ቢሊየን በላይ ኢንቨስት በማድረግ የትምህርት ጥራትና ተደራሽነትን ለማረጋገጥ እድሚያቸው ለትምህርት የደረሱ ተማሪዎች ዕድል እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል።

የጤና ፖሊሲ ውጤታማ ከማድረግ እና ህብረተሰቡ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋጋጥ ለጤና ዘርፉ ብር 20.781 ቢሊየን ወጪ በማድረግ የእናቶች የሞት ምጣኔን እንዲቀንስ ፣ ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናትን ሞት ምጣኔ ትርጉም ባለው መልኩ ዝቅ ማድረግ ተችሏል።

መንግስት በብድር ለቤቶች ግንባታ እንዲውል ከሚያቀርበው በተጨማሪ የከተማ አስተዳዳሩ የቤቶች ልማት ስራው ተግባራዊ እንዲሆን ለመሰረተ ልማት ግንባታና በዝቅተኛ ወጪ ቤቶችን ለመገንባት ባለፉት ሶስት ዓመታት/2013-2015/ ከ14.361 ቢሊየን ብር በላይ ወጪ በማድረግ የ145,000 ቤቶችን ግንባታ በማጠናቀቅ ለተጠቃሚ ተደራሽ እንዲሆን አድርጓል። በዚህም በአንድ ቤተሰብ በአማካይ 5 ሰው 750 ሺህ የከተማው ነዋሪ ተጠቃሚ የተደረጉ ሲሆን ከዚህም ውስጥ የሴቶች ድርሻ ከፍተኛውን ይይዛል።

የከተማ አስተዳዳሩ ባለፉት ሶስት ዓመታት/2013-2015/ ብር 6.806 ቢሊየን ብር በላይ ወጪ በማድረግ የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት ፍላጎትና አቅርቦትን ለማጣጣም እና አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል ባደረገው ጥረት በዘርፉ የሚታየውን መጠነ ሰፊ ችግር በመቅረፍ ከፍተኛ ሊባል የሚችል ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል።

የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት የከተማ አስተዳዳሩ ለህብረተሰቡ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ በመንግስት እና በብድር በርካታ ስራዎችን ሰርቶ ለአገልግሎት አብቅቷል። በዚህም መሰረት ባለፉት ሶስት ዓመታት ከ 19.568 ቢሊየን ብር በላይ ወጪ በማድረግ የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን 55% እና የፍሳሽ አገልግሎት ደግሞ 29% ማድረስ ተችሏል። በ2016 በጀት ዓመትም ለነዚህ ዘርፎች ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን በጀት መድቦ ወደ ተግባር ተገብቷል።


የከተማ አስተዳዳሩን የ10 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድና የዜጎችን ቅድመ ፍላጎቶች መሰረት በማድረግ ከአጠቃላይ ለ2016 በጀት ዓመት ተደግፎ ከቀረበው የከተማ አስተዳደሩ የወጪ በጀት ውስጥ ብር 103.88 ቢሊየን ወይም 74.04 በመቶ ከፍተኛ የወጪ በጀት 13 ዘርፎች በአንጻራዊነት ትልቁን ድርሻ እንዲይዙ የተደረጉ ስትራቴጂክ ዘርፎች በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው።

- ለአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ.....ብር 19.391 ቢሊየን፣
- ለውሃና ፍሳሽ ዘርፍ..... ብር 13.46 ቢሊየን፣
- ለመንገድ ልማት ዘርፍ.....ብር 11.62 ቢሊየን፣
- ለዲዛይንና ግንባታ ስራዎች..... ብር 10.49 ቢሊየን፣

- ለትላልቅ ፕሮጀክቶች..... ብር 9.97 ቢሊየን
- ለጤና ዘርፍ.....ብር 8.55 ቢሊየን፣
- ፍትህ፣ሰላምና ጸጥታ ዘርፍ.....ብር 6.78 ቢሊየን፣
- ለቤቶች ልማት ዘርፍ.....ብር 6.07 ቢሊየን፣
- ለጽዳት አስተዳዳር ዘርፍ .....ብር 4.66 ቢሊየን
- ለትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ.....ብር 4.32 ቢሊየን
- የአረንጓዴ ልማት ዘርፍ.....ብር 4.23 ቢሊየን፣
- ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና ዘርፍ .....ብር 2.26 ቢሊየን እና
- ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ .....ብር 2.08 ቢሊየን ይጠቀሳሉ።

ግራፍ 2 በበጀት ምደባ ወቅት ትኩረት የተሰጥቷቸው ዘርፎች ከአጠቃላይ በጀት ያላቸው ድርሻ (በመቶኛ)

በ2016 በጀት ድልድል ከፍተኛ በጀት ከተደለደለላቸው ውስጥ አጠቃላይ ትምህርት 18.67 በመቶ የያዘ ሲሆን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ደግሞ 2.00 በመቶ ድርሻ ይዟል።



ምንጭ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ፋይናንስ IBEX ሪፖርት 2015 ዓ.ም

4.6.6.ልዩ ትኩረት የተሰጣቸውና ከፍተኛ በጀት የተመደበላቸው ድህነት ተኮር ፕሮግራሞች

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የበጀት ድልድሉ በዋናነት ድህነት ተኮር ዘርፎች ላይ ቢሆንም የህብረተሰቡን ኑሮ፣የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ፣እንዲሁም ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚፈጠረውን የስራ ዕድል ከግምት ውስጥ በማስገባት ከዚህ በታች ለቀረቡት ፕሮግራሞች ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ተደርጓል።

4.6.6.1. የከተማ ልማታዊ ሴፍቲ ኔት

ዜጎች ምርታማ እንዲሆኑና ከድህነት እንዲወጡ በመንግስት እና በዓለም ባንክ በጥምረት ባለፉት ሶስት ዓመታት እየተካሄደ ያለው የከተማ ምግብ ዋስትና ከድህነት ወለል በታች በሚገኙ 343,180 ነዋሪዎችን እሴት በሚጨምሩ የአካባቢ ልማት ስራዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርገዋል። በዚህ መሰረት ባለፈው 2014 በጀት ዓመት ለዚሁ ተግባር ብር 2.188 ቢሊየን ወጪ የተደረገ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት ፕሮግራሙ በአካባቢ ልማት 109,918፣በቀጥታ ድጋፍ 66,548፣ እንዲሁም ለወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ 10,500 በአጠቃላይ 186,966 ተጠቃሚዎችን አቅፎ ለዚህ ተግባር ከ1.5 ቢሊየን ብር በላይ በጀት የተያዘለት ሲሆን በያዝነው 2016 በጀት ዓመት ደግሞ ብር 1.9 ቢሊየን ብር ለዚሁ ፕሮግራም በጀት ተይዞ 201,391 የህብረተሰብ ክፍልን በአካባቢ ልማት እና በቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ ወደ ስራ ተገብቷል።

4.6.6.2. የተማሪዎች ምገባና የተለያዩ ድጋፎች

የከተማው አስተዳዳር ትኩረት አድርጎ ትምህርትን ለሁሉም በፍታዊነት ተደራሽ ለማድረግ ተቋማዊ አደረጃጀት በመፍጠር የተማሪዎች ምገባ መርሃ ግብር በ2012 ዓ.ም ለ382,410 ተማሪዎች የተጀመረ ሲሆን በ2014 በጀት ዓመት ከ650,000 በላይ ተማሪዎች ተጠቃሚ ተደርጓል። ከዚህ ባሻገር በምገባው ተግባር ላይ ለተሰማሩ 10 ሺህ ለሚጠጉ እናቶች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል። በተጠናቀቀው 2015 በጀት ከ 803,000 በላይ ተማሪዎች በመርሀ-ግብሩ እንዲታቀፉ የተደረገ ሲሆን ለዚህም ተግባር የከተማው አስተዳዳር 2.6 ቢሊዮን ብር ተመድቧል። በያዝነውም የ2016 በጀት ዓመት ደግሞ ለምገባ ብር 3,267,672,330.00 ተይዞዋል።

በሌላ በኩል ለተማሪዎች የደንብ ልብስ በ2014 በጀት 1.02 ቢሊየን ብር የተመደበ ሲሆን በተጠናቀቀው በ2015 በጀት ዓመት ደግሞ ብር 1.025 ቢሊየን ተይዞ ተግባር ላይ መዋሉ ይታወሳል። በያዝነው 2016 በጀት ዓመት ደግሞ ለዚሁ ተግባር ብር 1,921,469,240.00 ተመድቦ ወደ ተግባር ተገብቷል።

4.6.6.3. የአዲስ አበባ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት ድጎማ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የትራንስፖርት አገልግሎቱን ተገልጋዩ ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያደርጋቸው ኢንቨስትመቶች እንደተጠበቁ ሆነው ነዋሪው ህዝብ አገልግሎቶችን ኪሱን በማይጎዳና የኑሮ ጫናው እንዳያማርረው ታሳቢ ባደረገ መልኩ አገልግሎት እንዲያገኝ በመንገደኞች ቲኬት ላይ ድጎማ ሲያደርግ ቆይቷል። በዚሁ መሰረት የመንገደኞች ቲኬት ድጎማን በ2014 በጀት ዓመት ብቻ ለአውቶቡስ አገልግሎት ድጎማ ብር 532 ሚሊየን በ2015 በጀት ዓመትም ብር ከ 760 ሚሊየን በላይ ድጎማ የተደረገ ሲሆን በያዝነው 2016 በጀት ዓመት ደግሞ ብር 853.00 ሚሊየን ለዚህ ተግባር በጀት ተይዟል።

4.6.6.4. ለፐብሊክ ሰርቪስ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት

ለፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኛም የትራንስፖርት ችግርን በማቃለል ምርታማነታቸውንና አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል በ2014 በጀት ብር 534 ሚሊየን፣ በ2015 በጀት ዓመት ብር 660 ሚሊየን ለአገልግሎት ክፍያ ወጪ የተደረገ ሲሆን በያዝነው 2016 በጀት ዓመት ደግሞ ብር 910.00 ሚሊየን ለዚህ ተግባር በጀት ተይዟል።

4.6.6.5. ለአዲስ አበባ ቀላል ባቡር አገልግሎት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የትራንስፖርት አገልግሎቶችን አቅርቦትንና ተደራሽነትን ለማሻሻል ከኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን የአዲስ አበባ ቀላል ባቡርን የተረከበ ሲሆን ለዚህም አስተዳዳሩ 500 ሚሊዮን ብር የድጎማ በጀትየመደበ ሲሆን በያዝነው 2016 በጀት ዓመትም ዘርፉን ውጤታማ ከማድረግ አንጻር ብር 500 ሚሊየን በጀት መድቦ ወደ ተግባር ተብቷል።

4.6.6.6. ለሸገር ዳቦና ለሸማቾች ማህበራት የሚሰጥ ድጎማ (የገንዘብ ድጋፍ)

የከተማ አስተዳዳሩ ነዋሪው ህብረተሰብ በኑሮ ውድነት ምክንያት የሚታየውን ጫና ለመቀነስ ለሸገር ዳቦ አቅርቦትን በዝቅተኛ ዋጋ እንዲቀርብ እና የምግብ ሸቀጦችንና መሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦትን ለመደጎም በመቶ ሚሊየን ብር ድጎማ አድርጓል። በመሆኑም በ2014 በጀት ዓመት ለሸማቾች ማህበራት የገበያ ማረጋጊያ ብር 500 ሚሊየን እንዲሁም ለሸገር ዳቦ ብር 375 ሚሊየን ብር ድጎማ ተደርጓል። በተጨማሪም በ2015 በጀት ዓመት ለሸገር ዳቦ ብር 350 ሚሊየን ተመድቦ የነበረ ሲሆን በያዝነው 2016 በጀት ዓመት ለዚሁ ተግባር ደግሞ ብር 400.00 ሚሊዮን ድጋፍ በጀት እንዲያዝ ተደርጓል።

4.7. ገቢን ከማሳደግና ወጪን ከመቆጠብ አኳያ የተወሰዱ አዳዲስ የፖሊሲ እርምጃዎች

የከተማ አስተዳዳሩ የፊስካል ፖሊሲ የሚያተኩረው በዋናነት ገቢን በማሳደግ ወጪን ቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም ላይ ነው። በዚህ ረገድ በከተማ አስተዳደሩ በርካታ የፖሊሲ እርምጃዎችን በመውሰድ ውጤታማ አፈጻጸም አስመዝግቧል። ባለፉት ሶስት ዓመታት(2013-2015) ገቢን ከማሳደግ አኳያ ከተወሰዱ እርምጃዎች መካከል የመንግስት መስሪያ ቤቶች አገልግሎት ክፍያ ማሻሻያ፣ የቤት ገቢ ግብር፣ የቤት ሽያጭ ገቢ ግብር በዋነኝነት የሚጠቀሱ ሲሆን በአንጻሩ የወጪ ቅነሳ መመሪያ ማውጣት፣ ወጪን በኖርም መገደብ እና የቢሮ ኪራይ ወጪን ለመቀነስ የአስፈጻሚ ተቋማት ማዕከላዊ በሆኑ አካባቢ ህንጻን በጋራ እንዲከራዩ ማድረግ ወጪን ከመቆጠብ ጋር በተያያዘ ከተወሰዱ እርምጃዎች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው።

በ2016 በጀት ዓመትም ገቢን ለማሳደግና ወጪን ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት በተጠናከረ መልኩ የሚቀጥል ሲሆን በዚህም መሠረት የሚከተሉትን እርምጃዎች ለመውሰድ ታቅዷል፡-

- የገቢ አቅም (Revenue Potential) ጥናት ወደ ተግባር ማስገባት፣
- የቤት ገቢ ግብር፣ የቤት ሽያጭ ገቢ ግብር በተጠናከረ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የመንግስት አገልግሎት ክፍያ ተመን ማሻሻያ፣
- የገቢ አፈጻጸምን ለማሳደግ የተጀመረው የገቢ ግብረ ሀይል ንቅናቄ አደረጃጀት አጠናክሮ ማስቀጠል፣
- የወጪ ትንተና ጥናት ላይ በመመስረት የወጪ ቁጠባ መመሪያን አዘጋጅቶ ማስፈጸም ፣

የበጀትና ፋይናንስ ቴክኒካል ቃላቶችና ሀረጎች መግለጫ

1) **የአስተዳደር ስልጣን:-** በመንግስት አስተዳደር ከከተማ አስተዳዳር እስከ ወረዳ ድረስ ያለው የስልጣን ተዋረድ ማለት ነው።

2) **የበጀት ዑደት፡-** በመንግስት በጀት አስተዳዳር ስርዓት ውስጥ የሚካተቱ ዋና ዋና ተግባራትን በጀት ማዘጋጀት፣ማጸደቅ፣ሥራ ላይ ማዋል እና ኦዲት እና ግምገማ በቅደም ተከተል/በደረጃ የሚያመለክት ነው።

3) **የበጀት ጥሪ፡-** በፋይናንስ ቢሮ የተዘጋጀና ባለበጀት መ/ቤቶችም በተቀመጠው የበጀት ማዘጋጃ መመሪያ መሰረት ለመ/ቤታቸው እቅድ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጋቸውን በጀት አዘጋጅተው እንዲቀርቡ ማሳሰብ ነው።

4) **የበጀት ጥያቄ፡-** የመንግስት ተቋማት ከፋይናንስ ቢሮ በተላለፋቸው የበጀት ጥሪ መሰረት ያስፈልገኛል ያለውን የበጀት አመቱን የወጪ አይነት በዝርዝር ለፋይናንስ ቢሮ የሚያቀርበው ጥያቄ ነው።

5) **የበጀት ድጎማ፡-** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ለተቋማት/ክፍለ ከተሞች የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍ ነው።

6) **የካፒታል ወጪ፡-** በተቋማት የመንግስትን አገልግሎት ለመስጠትና ለማሻሻል ቋሚ ሀብት ለማፍራት ወይንም ለማሻሻል የሚውል ወጪ ነው።

7) **የዜጎች በጀት፡-** መሠረታዊ የበጀት መረጃዎች ዜጎች ሊረዱት በሚችሉ ቀላል እና ግልፅ በሆነ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ተደራሽ የሚደረግ የበጀት መረጃ ሰነድ ነው።

8) **የዜጎች ሁለንተናዊ ተሳትፎ፡-** ከመንግስት የሚሰጡ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ለማሻሻል ዜጎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በእቅድ ዝግጅት፣ ትግበራና የአፈፈፃፀም ግምገማ ላይ የሚያደርጉትን ሁለንተናዊ ተሳትፎን ያመለክታል።

9) **የከተማ አስተዳደሩ የራስ ገቢ፡-** መንግስት የበጀት ዓመቱን ወጪ ለመሸፈን የከተማው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከታክስ፣ ታክስ ካልሆኑ እና ማዘጋጃቤታዊ ገቢዎች የሚሰበስበው የሚያመለክት ነው።

10) **የኢኮኖሚ መረጋጋት፡-** የማክሮ ኢኮኖሚው ከመጠን በላይ አለመለዋወጥና በተከታታይነት የማያቋርጥ የዕድገት መጠን፣ ዝቅተኛ እና የተረጋጋ የዋጋ ግሽበት ያለው ኢኮኖሚ ማለት ነው።

11) **የውጭ እርዳታ፡-** በመንግስት አቅም ሊሸፈኑ የማይችሉትን መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለመደገፍና ለማገዝ ከሚፈልጉ የውጭ መንግስታትና እርዳታ ድርጅቶች የሚገኝ ሀብትን የሚያጠቃልል ሲሆን በዚህ ሰነድ አውድ የፌደራል መንግስት ከላይ በተገለጸው መልኩ ከሚያገኘው ሀብት ለከተማ አስተዳደሩ የሚመድበውን ድርሻ ያመለክታል።

12) **የውጭ ብድር፡-** መንግስት የወጪ ግዴታውን ለመወጣት የሚያስፈልገውን ሀብት ከሀገር ውስጥ ከሚገኝ የበጀት ምንጭ መሸፈን በማይችልበት ሁኔታ የበጀት ጉድለቱን ለማሟላት ከውጭ አበዳሪዎች የሚገኘውን ሀብት ሲሆን በዚህ ሰነድ ዐውድ የፌደራል መንግስት ከላይ በተገለጸው አግባብ ከሚያገኘው ሀብት ለከተማ አስተዳደሩ የሚመድበውን ድርሻ ያመለክታል።

13) **የበጀት ዓመት፡-** በመላ ሀገሪቱ ወጥ የሆነና በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር መሰረት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ድረስ ያሉትን 12 ወራት የሚሸፍን የበጀት ትግበራ ጊዜ ማለት ነው።

14) **የፊስካል ፖሊሲ፡-** መንግስት ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠር የመንግስት ገቢ አሰባሰብና ወጪ አደረራረግ የሚመራበት ስርዓት ነው።

15) **የፋይናንስ ሀብት/ገቢ፡-** መንግስት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚውሉ ወጪዎችን ለመሸፈን ከታክስ፣ ታክስ ካልሆኑና ከሌሎች የገቢ ምንጮች የሚገኘው ገንዘብ ማለት ነው።

16) **የመካከለኛ ጊዜ የወጪ ማዕቀፍ፡-** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የሦስት ዓመት የወጪ ዕቅዶችን ያወጣል፣ በጀቶች የመንግስትን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የሚያንፀባርቁ እና ለመንግስት መልሶ ግንባታ እና ልማት ግዴታዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግ ያለመ ነው።

17) **ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት፡-** በአንድ የተወሰነ ጊዜ ውስጥ በአንድ ሀገር ውስጥ የተደረጉ ከሁሉም ከተጠናቀቁ ምርትና አገልግሎቶች የተገኘ የገንዘብ ዋጋ ነው።

18) **የዋጋ ግሽበት/ንረት መጠን፡-** አሁን ያለውን የሸቀጦትና አገልግሎቶች ዋጋ ከዚህ በፊት ከነበረው ዋጋ ጋር በማነጻጸር የዋጋ ለውጡን በመቶኛ መስቀመጥ ነው።

19) **ማክሮ ኢኮኖሚ፡-** የአጠቃላይ ወይም ጥቅል ሀገራዊ ኢኮኖሚው አወቃቀር፣ አፈፃፀም፣ ባህሪንና የውሳኔ አሰጣጡን የሚያመለክት ነው።

20) የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ፡- አመታዊ የፊዝካል ዕቅዶችና ግቦች የፖሊሲ ትግበራ አማራጮች የሚወሰኑበት እንዲሁም ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የበጀት ዓመቱ የገቢና ወጪ ግምት የሚከናወንበት ማዕቀፍ ነው።

21) **ፖሊሲ፡-** በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውና ሊተገበሩ የታቀዱ ውጥኖች ማስፈፀሚያ መመሪያ ነው።

22) **ቅድመ-በጀት ውይይት፡-** በወረዳ ደረጃ የዜጎችን የመሰረታዊ አገልግሎቶች ቅድመ-ፍላጎቶችና ምርጫዎች በዕቀድ ለማካተትና ለማከናወን ከወረዳው የተለያዩ የማህበረሰበ ክፍሎች ከተወከሉ ነዋሪዎች ጋር የሚደረግ ውይይት ነው።

23) **ቅድመ-በጀት መግለጫ፡-** በበጀት ዓመቱ በመንግስት አስፈጻሚ አካላት የሚዘጋጀዉ የበጀት ፕሮፖዛል ለህግ አዉጭዉ አካል (የከተማዉ ም/ቤት) ቀርቦ ከመጽደቁ በፊት አስፈጻሚዉ አካል ባቀረበዉ ረቂቅ ላይ ውይይትና ክርክር የሚያድርግበት እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው የማህበረሰብ ተወካዮች፣ ተቋማትና ግለሰቦች አስተያየት የሚሰጡበት እና በዚህም መሠረት ማስተካከያ የሚደረግበት መግለጫ ነው።

24) **የመንግስት ተቋማት (የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች)፡-** በከተማ አስተዳደሩ በአዋጅ የተቋቋመና ሙሉ በሙሉም ይሁን በከፊል ከመንግስት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደርንና የፋይናንስ እንቅስቃሴው በመንግስት ቁጥጥር የሚደረግበትን ማንኛውንም መ/ቤት ወይም ተቋም ያካትታል።

25) **መደበኛ በጀት፡- ቋሚ** ንብረቶችን ለመፍጠር የማይውልና መንግስታዊ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚዉል በጀት ሲሆን ይህም ለደመወዝ ክፍያ እና ለዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚዉሉ ወጪዎችን የሚያካትት ነው።

26) **ተንከባላይ ወጪ፡-** ከአንዱ በጀት ዓመት ወደ ሚቀጥለው የሚንከባለልና በየጊዜው የሚታደስ ወጪን ያመለክታል።

27) **ዘላቂ የልማት ግቦች፡-** ለሁሉም የተሻለ እና ቀጣይነት ያለው ምቹ ሁኔታን ለመፍጠርና ዓለም ዓቀፍ ተግዳሮቶች ማለትም ድህነትን፣ ኢ-ፍትሃዊነትን፣ የአየር ንብረት ለውጥንና የአካባቢ ብክለትን ለመቅረፍ እንዲሁም ሰላምን ለማስፈን የተወጠኑ ዓለም አቀፍ ግቦች ናቸው።

ማጣቀሻ/ዋቢ

- **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር** 74/2014
- **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የፍኖተ-ብልጽግና ማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ** 2013
- **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ ጥናት** (2016-2018)
- **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የ**2016 **በጀት ዓመት የበጀት አዋጅ**
- **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ፋይናንስ ቢሮ የገቢና ወጪ ሪፖርት** (2013-2015)
- **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ አዘገጃጀት መመሪያ** 2014 **ዓ.ም**
- **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የበጀት ማኑዋል** 2006 **ዓ.ም**
- **የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት አንቀጽ** 89 **ንዑስ አንቀጽ** 6 1987
- **የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማቋቋሚያ ቻርተር አዋጅ ቁጥር** 361/1995
- **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር** 51/2009
- **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓት መተግበሪያ መመሪያ ቁጥር** 05/2011
- http://www.un.org/sustainabledevelopment/news/communications-material/

ለበለጠ መረጃ፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማ ፋይናንስ ቢሮ
አዲስ አበባ/ ኢትዮጵያ
ስልክ:-መደበኛ፡ +251 ; **ሞበይል**: +251-913284645;
ኢ-ሜይል፡ belete1985@gmail.com